በእስራኤል ላይ የበየነውን ፍርዱን ፈጸመ::”
[22]ስለ ዳንም እንዲህ አለ:-
“ዳን ከባሳን ዘሎ የሚወጣ፣
የአንበሳ ደቦል ነው::”
[23]ስለ ንፍታሌምም እንዲህ አለ፤
“ንፍታሌም *በእግዚአብሔር* (ያህዌ) ሞገስ
ረክቶአል፤
በበረከቱም ተሞልቶአል፤
ባሕሩንና የደቡብን ምድር ይወርሳል::”
[24]ስለ አሴርም እንዲህ አለ:-
“አሴር ከሌሎች ልጆች ይልቅ የተባረከ
ነው፤
በወንድሞቹ ዘንድ ተወዳጅ ይሁን፤
እግሩንም በዘይት ውስጥ ያጥልቅ::
[25]የደጃፍህ መቀርቀሪያ ብረትና ናስ
ይሆናል፤
ኀይልህም በዘመንህ ሁሉ ይኖራል::
[26]“አንተን ለመርዳት በሰማያት ላይ፣
በግርማው በደመናትም የሚገሠግሥ፣
እንደ ይሹሩን አምላክ (ኤሎሂም) ያለ ማንም የለም::
[27]ዘላለማዊ አምላክ (ኤሎሂም) መኖሪያህ ነው፤
የዘላለም ክንዶቹም ከሥርህ ናቸው፤
‘እርሱን አጥፋው!’ በማለት፣
ጠላትህን ከፊትህ ያስወግደዋል::
[28] ስለዚህ እስራኤል ብቻውን በሰላም
ይኖራል፤
የሰማያት ጠል በሚወርድበት፣
እህልና የወይን ጠጅ ባለበት ምድር፣
የያዕቆብ ምንጭ የሚነካው የለም::
[29]እስራኤል ሆይ፤ አንተ ቡሩክ ነህ፤
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ያዳነው ሕዝብ፣
እንዳንተ ያለ ማን አለ?
እርሱ ጋሻህና ረዳትህ፣
የክብርህም ሰይፍ ነው::
ጠላቶችህ በፍርሀት ከፊትህ
ያፈገፍጋሉ፤
አንተም የማምለኪያ ኰረብታቸውን መረ
ማመጃ ታደርጋለህ::”

### የሙሴ መሞት

34 ሙሴ ከሞአብ ሜዳ ተነሥቶ ለኢ
ያሪኮ ትይዩ ወደ ሆነው ፊስጋ
ጫፍ፣ ወደ ናባው ተራራ ወጣ:: በዚያም
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ምድሪቱን ሁሉ አሳየው፤
ይኸውም ከገለዓድ እስከ ዳን፣ [2]ንፍታሌምን
ሁሉ፣ የኤፍሬምንና የምናሴን ግዛት፣ እስከ
ምዕራብ ባሕር[†] ድረስ ያለውን የይሁዳን
ምድር ሁሉ፣ [3]ኔጌብንና የዘንባባ ከተማ
ከሆነችው ከኢያሪኮ ሸለቆ እስከ ዞዓር
ያለውን ምድር ሁሉ ነው:: [4]ከዚያም በኋላ
*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ሙሴን “ለአብርሃም፣
ለይስሐቅና ለያዕቆብ፣ ‘ለዘሮቻችሁ እሰጣለሁ’
ብዬ በመሐላ ቃል የገባሁላቸው ምድር
ይህች ናት:: በዐይንህ እንድታያት አድርጌአ
ለሁ፤ ነገር ግን ወደዚያ አትሻገርም” አለው::
[5]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) እንደ ተናገረው *የእግ
ዚአብሔር* (ያህዌ) አገልጋይ ሙሴ በሞዓብ
ምድር ሞተ:: [6]በሞዓብ ምድር በቤተ ፌጎር
ፊት ለፊት ባለው ሸለቆ ቀበረው[‡]፤ ይሁን
እንጂ መቃብሩ የት እንደ ሆነ እስከ ዛሬ
ማንም አያውቅም:: [7]ሙሴ በሞተ ጊዜ ዕድ
ሜው መቶ ሃያ ዓመት ነበር፤ ሆኖም ዐይኑ
አልፈዘዘም፤ ጒልበቱም አልደከመም:: [8]የልቅ
ሶውና የሐዘኑ ጊዜ እስኪያበቃ ድረስ እስራ
ኤላውያን በሞዓብ ሜዳ ሠላሳ ቀን አለቀ
ሱለት::
[9]ሙሴ እጆቹን ጭኖበት ነበርና፣ የነዌ
ልጅ ኢያሱ በጥበብ መንፈስ ተሞላ:: ስለዚህ
እስራኤላውያን አደመጡት፤ *እግዚአብሔር*
(ያህዌ) ሙሴን አዞት የነበረውንም ሁሉ አደ
ረጉ::
[10]*እግዚአብሔር* (ያህዌ) ፊት ለፊት ያወቀው
እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ከዚያ ወዲህ በእ
ስራኤል አልተነሣም፤ [11]*እግዚአብሔር* (ያህዌ)
ልኮት፣ እነዚያን ታምራዊ ምልክቶችና ድን
ቆች ሁሉ በግብፅ በፈርዖን፣ በሹማምቱና
በምድሪቱ ሁሉ ላይ እንዲያደርግ የላከውን
ያደረገ ማንም ሰው አልነበረም፤ [12]ሙሴ በእ
ስራኤል ሁሉ ፊት ያሳየውን ታላቅ ኀይል
ያሳየ ወይም ያደረገውን አስፈሪ ተግባር የፈ
ጸመ ማንም ሰው የለም::

33፥22 ዘኍ1፥38፤ 49፥16
33፥23 ዘፍ30፥8
33፥24 ዘፍ30፥13፤ 49፥20፤ዘዳ32፥13
33፥25 ዘዳ32፥47፤ ነህ3፥3፤7፥3፤ መዝ147፥13
33፥26 ዘፀ15፥7፤ ዘዳ10፥14፤32፥15፤ 2ሳሙ22፥10፤ መዝ18፥9፡10፤68፥4፡ 33፤104፥3፤ዳን7፥13
33፥27 ዘፍ21፥33፤ ዘፀ15፥18፤34፥11፤ ዘዳ7፥2፤ኢሱ24፥18፤ መዝ9፥9፤84፥1፤ 90፥1፤91፥9፤ ኢሳ40፥28፤57፥15
33፥28 ቀኍ13፤ ዘፍ27፥28፤ዘፀ33፥16፤ ዘሌ25፥18፤ዘዳ32፥8፤ መዝ16፥9፤ምሳ1፥33፤ ኢሳ14፥30፤
33፥29 ዘፍ15፥1፤ ዘፀ18፥4፤ዘኍ33፥52፤ ዘዳ4፥7፤32፥13፤ 2ሳሙ22፥45፤ መዝ1፥1፤10፥14፤ 18፥1፡44፤27፥1፡9፤ 30፥10፤32፥1-2፤54፥4፤ 66፥3፤70፥5፤81፥15፤ 115፥9-11፤118፥7፤ 144፥15፤ኢሳ45፥24፤ ሆሴ13፥9፤ዕን3፥19
34፥1 ዘፍ14፥14፤ ዘኍ21፥20፤32፥3፤ ዘዳ32፥49፡52፤
34፥2 ዘፀ23፥31
34፥3 ዘፍ12፥9፤ 13፥10፤2ዜና28፥15፤ መሳ1፥16፤ 3፥13
34፥4 ዘፍ12፥7፤ 28፥13፤ዘዳ3፥23፤ ኢሱ21፥43
34፥5 ዘፍ25፥8፤ ዘኍ12፥7፤
34፥6 ዘዳ3፥29፤ ይሁ1፥9
34፥7 ዘፍ15፥15፤ 27፥1፤ዘፀ7፥7
34፥8 ዘፍ37፥34፤ ዘኍ21፥11፤ዘዳ1፥3፤ 2ሳሙ11፥27
34፥9 ዘፍ41፥38፤ ዘፀ28፥3፤ዘዳ31፥14፤ ኢሳ11፥2፤ሐሥ6፥6
34፥10 ዘፍ20፥7፤ ዘፀ33፥11፤ዘዳ18፥15፡18
34፥11 ዘፀ11፥3፤ ዘዳ4፥34 34፥12 ዘዳ4፥34፤ዕብ3፥1-6፤

[†]2 ይኸውም የሜዲትራንያን ባሕር ነው::
[‡]6 ወይም፣ *ተቀበረ* ተብሎ መተርጐም ይቻላል::